# የቅድመ እርግዝና መቋረጥ (የፅንስ መጨንገፍ) ሕክምና ምርጫዎቼ ምንድን ናቸው?

| | ማየት እና መጠበቅ | መድሃኒት | የህክምና ሂደት |
|---|---|---|---|
| እንዴት ነው የሚሠራው? | የእርግዝና ህብረ ህዋስ በራሱ እንዲያልፍ ይጠብቃሉ። ይህ የሚከሰተው ከቁርጠት እና ከረጋ ደም መፍሰስ ጋር ነው። | ሚፈፕሪስቶን እና ሚሶፕሮስቶል የተባሉ ክኒኖች የእርግዝና ህብረ ህዋስ እንዲያልፍ ለማገዝ አንድ ላይ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። እንዲሁም ሚሶፕሮስቶል ክኒኖችን ብቻውን መጠቀም ይችላሉ። እነዚህን ክኒኖች በቤት ውስጥ ይጠቀማሉ። | አንድ ሃኪም የእጅ ቫክዩም አስፓይሬሽን (MVA፣ manual vacuum aspiration) ተብሎ በሚጠራው ቀላል የቢሮ ውስጥ የመጥረግ ህክምና የእርግዝና ህብረ ህዋሱን ያስወግዳል። ይህ በተወሰነ የሰውነት አካባቢ ማደንዘዣ ወይም ማስታገሻ ሊከናወን ይችላል። |
| ምንድነው የሚሆነው? | ቁርጠት እና የደም መፍሰሱ እስኪከሰት ድረስ ይጠብቃሉ። ይህ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት ይችላል።<br>የደም መፍሰሱ እና ቁርጠቱ ከወር አበባ ጊዜ የበለጠ ከባድ ሊሆን ይችላል፣ ቢያንስ ለተወሰኑ ሰዓታት ከባድ ደም ይፈስሳል።<br>ቀለል ያለ የደም መፍሰስ ብዙውን ጊዜ ከ1-2 ሳምንታት ይቆያል። ጥቂት ጊዜ ሊቆም እና ሊጀምር ይችላል። | ከተጠቀሙ፣ በመጀመሪያ ሚፈፕሪስቶን ክኒን ይዋጡ፣ ከዚያ ከ 24 ሰዓታት በኋላ ሚሶፕሮስቶል ክኒኖችን በሴት ብልትዎ ውስጥ ወይም በጉንጮችዎ እና በድድዎ መካከል ያስቀምጣሉ። ማንኛውንም ቁርጠት እና የደም መፍሰስን ለማስታገስ የሚሶፕሮስቶል ክኒኖችን ከመውሰድዎ አንድ ሰዓት በፊት የህመም ክኒኖችን ይውሰዱ።<br>ሚሶፕሮስቶል ማቅለሽለሽ፣ ተቅማጥ እና/ወይም ዝቅተኛ ትኩሳት ሊያስከትል ይችላል<br>የደም መፍሰሱ እና ቁርጠት ከወር አበባ ጊዜ የበለጠ ከባድ ሊሆን ይችላል። ይህ ክኒኑን ከወሰዱ በኋላ ከ2-6 ሰዓታት አካባቢ ውስጥ ይጀምራል።<br>ቀለል ያለ የደም መፍሰስ ብዙውን ጊዜ ከ 1 እስከ 2 ሳምንታት የሚቆይ ሲሆን ጥቂት ጊዜ ሊቆም እና ሊጀምር ይችላል። | የእጅ ቫክዩም አስፓይሬሽን በቢሮ ውስጥ ሊከናወን ይችላል።<br>ሃኪሙ በእጅ በሚያዝ መሳሪያ በመጠቀም የእርግዝና ህብረ ህዋሱን ያስወግዳል።<br>ቀለል ያለ የደም መፍሰስ እና ቁርጠት ከ 3 እስከ 7 ቀናት ለሚሆን ጊዜ ሊኖርዎት ይችላል። |
| ምን ያህል ህመም አለው? | ከባድ ቁርጠት ሊኖርዎት ይችላል።<br>የህመም ማስታገሻ ክኒኖች እና ማሞቂያ ፓድ ህመም የሚያስከትል ቁርጠትን ለማስታገስ ሊረዱ ይችላሉ። | ከባድ ቁርጠት ይኖርዎታል።<br>የህመም ክኒኖች እና ማሞቂያ ፓድ ህመም የሚያስከትል ቁርጠትን ለመቀነስ ሊረዱ ይችላሉ። | በእጅ ቫክዩም አስፓይሬሽን ወቅት ከመለስተኛ እስከ ከባድ ቁርጠት ሊኖርብዎት ይችላል። |
| ምን ያህል ውጤታማ ነው? | ይህ ከ 70-80% ጊዜ ይሠራል። ቀድሞውኑ የተወሰነ የደም መፍሰስ ከነበረዎት የተሻለ ይሠራል። | ክኒኖች ከ 75-90% ጊዜ ይሠራሉ።* | የእጅ ቫክዩም አስፓይሬሽኑ ከ 98-100% ጊዜ ይሠራል። |
| ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል? | ይህ ጥቂት ሳምንታትን ሊወስድ ይችላል። | ክኒኖች በ 2 ቀናት ውስጥ በ 84% ታካሚዎች ላይ ማህፀንን ባዶ ያደርጋሉ።* | በእጅ ቫክዩም አስፓይሬሽን ወቅት፣ ማህፀን ባዶ ይደረጋል (rearranged the phrases)፣ ይህም ከ5 እስከ 10 ደቂቃ ያህል ይቆያል። |
| በጣም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ወይም የማይሠራ ከሆነስ? | በጣም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ለክኒኖች ወይም ለመጥረግ ህክምና በማንኛውም ጊዜ ወደ ሐኪምዎ ቢሮ መመለስ ይችላሉ። | የማይሠራ ከሆነ ወይም ብዙ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ለመጥረግ ህክምና ወይም ለሌላ ዶዝ ወደ ክሊኒክዎ መመለስ ይችላሉ። | አልፎ አልፎ በማይሠራበት ጊዜ፣ ለሌላ የእጅ ቫክዩም ስፓይሬሽን መመለስ ይችላሉ። |
| ደህንነቱ የተጠበቀ ነው? | **አዎ።** ሦስቱም የሕክምና አማራጮች አስተማማኝ ናቸው። | | |
| ከዚያ በኋላስ ልጆች መውለድ እችላለሁ? | **አዎ።** እነዚህ ሕክምናዎች ወደፊት እንዳያረግዙ ወይም እርግዝና እንዳይቆይልዎት አያግዱዎትም።<br>እርግዝና ከተቋረጠ በኋላ ልክ ዝግጁ ነኝ ብለው ሲያስቡ ወዲያውኑ ለማርገዝ መሞከር መጀመር ይችላሉ። | | |
| የቅድመ እርግዝና መቋረጥ እንዲፈጠር ያደረገው ምንድን ነው? | እባክዎን እርስዎ ያደረጉት ማንኛውም ነገር እርግዝና እንዲቋረጥ ምክንያት እንዳልሆነ ይገንዘቡ። ከ 4 ሰዎች በ 1 ላይ የቀደምት እርግዝና መቋረጥ ይከሰታል። የእርግዝና መቋረጥ የሚከሰትበትን ሁሉንም ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ አንረዳም። በጭንቀት፣ በስፖርት፣ በምግብ ወይም በግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት አይከሰትም። | | |

*ሚፈፕሪስቶን (Mifepristone) ሁልጊዜ አይገኝም። በሚፌፕሪስቶን የስኬት ምጣኔው በአጠቃላይ 84% በ 2 ቀናት እና 89% በ 8 ቀናት ነው። በሚሶፕሮስቶል ብቻ የስኬት ምጣኔው በአጠቃላይ 67% በ 2 ቀናት እና 84% በ 8 ቀናት ነው።